# ቅዱስ ጋብቻ

ጋብቻ የሚለው የአማርኛ ቃል ለኑሮ ለትዳር መግባባት፣ መስማማት፣ አንድ መሆን፣ መጣመር፣ መዋሐድ ማለት ነው። በመሆኑም የሁለት ተቃራኒ ጾታዎች ሕብረ ት ወይንም ጥምረት ጋብቻ ይባላል። ዘፍ. 2፥23። የወንድ ልጅ እና የሴት ልጅ በጋብ ቻ በአንድነት መኖር በየትኛውም ሕብረተሰብ ዘንድ የተወደደና የተከበረ የኑሮ መልክ እና ሥርዓት ነው። ያ ሊሆን የቻለው መሠረቱ በሰው ፈቃድ ላይ ብቻ ሳይሆን በእግ ዚአብሔር ፈቃድ መነሻነት የተመሠረተ በመሆኑ ነው።

የጋብቻ ሥርዓትን የሠራው የጋብቻንም ሕግ የደነገገው እግዚአብሔር ነው። የ ሁለት ተቃራኒ ሰዎች መፈጠር ጋብቻን ሕያው አድርጎታል። በመጀመሪያው የመጸሐፍ ቅዱስ ክፍለ ንባብ በመጀመሪያው ገጽ ላይ እንደምናነበው ከሰው ልጅ መፈጠር በኋላ የሰው ልጅ መጀመሪያ የተባረከበት በረከት ጋብቻ ነበር። ታሪኩም እንዲህ ይላል «እ ግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ወንድ እና ሴት አድረጎ ፈጠራቸው። እግዚአብሔርም ባረካቸው እንዲህም አላቸው ብዙ ተባዙ ምድ ርንም ሙሏት» ዘፍ 1፥27-28 ይህም ቃል የሚያመለክተው የአንዱ ሰው ለሌላው ሰው መፈጠር እና የሁለቱ ፍጡራን በጋብቻ አንድ ሆኖ መኖር የእግዚአብሔር በረከት መ ሆኑን ነው። ሰሎሞንም ለሰው ልጅ በዓላማና በሕይወት የሞትመስለውን የትዳር ጓደኛ ማግኘት በመጀመሪያው የኤደን በረከት መባረክ መሆኑን «ሚስትን ያገኘ በረከትን አ ገኘ። ከእግዚአብሔርም ሞገስን ይቀበላል» ብሏል። ምሳ 18፥22

## የትዳር ዓላማዎች

1. በምድር ላይ ዘር ለመተካት፣ የእግዚአብሔር ፍጥረት መገልጫ ለመሆን፣ የ እግዚአብሔር ሰው መገኛ ምንጭ ለመሆን ነው። ዘፍ 1፤27-28
2. በኑሮ ሁሉ ለመተጋገዝ፣ ለመተዛዘን፣ ለመረዳዳት አንዱ የሌላውን ሸክም እ ንዲያቀል፣ አንዱ ለሌላው እንዲያስብ፤ አንዱ ሌላውን ኃዘኑን እንዲያስረሳ ው እንዲያስደስተው ነው። ዘፍ 2፤18-25
3. በጾታው የሰው ልጅ እግዚአብሔርን እንዳይበድል እንደ እንስሳ እንዳይሆን እያንዳንዱ የራሱ የሆነ አካል እንዲኖረው ነው፤ 1ኛ ቆሮ 7፥1-7

<u>አንባቢ ሆይ</u>

ሰውነታችን ክቡር የእግዚአብሔር መቅደስ በመሆኑ እንደ እንስሳት ልቅ በሆነ አኗኗር ልንኖር አይገባም። የሰው ልጅ መቅድስ ሰውነቱን በንጽህና፣ በቅድስና ሊጠብ ቀው ይገባል። የንጽህና እና የቅድስና ሕይወት ማለት ደግሞ በትዳር ተወስኖ ከዝሙት እርቆ ንጽህናን ጠብቆ በዓላማ መኖር ነው። በዕጣት ከሚቆጠሩ በተፈጥሮ ምክንያት ወይንም ለተለየ ዓላማ በመንፈስ ቅዱስ ትዕዛዝ በተባህትዎ እንዲኖሩ ከተፈቀደላቸው ሰዎች በቀር (ማቴ. 19፥7-12,) 1 ቆሮ. 7) እንዲሁ መኖር ትርፉ እግዚአብሔርን በፈጠ ረው አካል ማሳዘን እና ያልተባረከ ኑሮ መኖር በመሆኑ በጋብቻ ተወስኖ ሕይወትን በቅ ድስና መምራት ይገባል። እኛ የሰው ልጆች እግዚአብሔር በአካላችን ካከበርነው እግ ዚአብሔርም ለእኛ የማያካፍለው ምሥጢር አይኖርም። የማይታደለን ኃይልም የለም። የማይፈጽምልን ተስፋም የለም። አብርሃም በትዳር የሚኖር የእግዚአብሔር ነቢይ ነበ ር። ምድርም በእርሱ ዘር ለመባረክ በቅታለች። ራሱን ለፈጣሪው መስዋዕት አድርጎ የ ሚቀርብ ልጅ ይስሐቅንም ያፈራው በቅዱስ ጋብቻ ነበር። እግዚአብሔርም «አብርሃ ም ፍቁርዬ» «አብርሃም ወዳጄ» ይለው ነበር። ይስሐቅ እንደ አባቱ የአባቶች አባት

ለመሆን የበቃ የእግዚአብሔር ወዳጅ እግዚአብሔር «ይስሐቅ ቍልኤዬ» «ይስሐቅ ወዳጄ» እያለ ይጠራው ነበር። ከአምላኩ ጋር የታገለው ያዕቆብም በትዳር የሚኖር የእግዚአብሔር ቅዱስ ነበር። እኛም ዛሬ «ወያዕቆብ ቅዱስከ» እያልን እግዚአብሔርን

የምንማጸንበት ቅዱስ ለመሆን የበቃው በቅዱስ ኑሮ በመኖሩ ነበር።

ከእግዚአብሔር ጋር የኖረው ቃል በቃል የተነጋገረው የእግዚአብሔር ራዕይ የታደለው እግዚአብሔርም እንደ ሙሴ ያለ የዋህ የለም ብሎ የመሰከረለት ሕዝቡንም ነጻ እንዲያወጣ ለአገልግሎት የጠራው ሙሴ በቅዱስ ትዳር (ጋብቻ) ይኖር ነበር። ካህኑ አሮን በቅዱስ ጋብቻ ይኖር ነበር። በጠቅላላ ብዙ የእግዚአብሔር ሰዎች በቅዱስ ኑሮ ለመኖር ያለፉበት የቅድስና መንገድ ጋብቻ ነበር። ስለዚህ የሰው ልጅ በቅዱስ ጋብቻ በመወሰን ከዝሙትም በመራቅ ከእግዚአብሔር ጋር መኖር ያሻዋል። ቅዱስ ሆኖ ቅዱሳንንም ወልዶ ወደ እግዚአብሔር መሄድ አለበት።

ጋብቻን ለፍጻሜ የሚያበቃው ዋና ነገር ደግሞ በሁለቱ ሰዎች መካከል ፍጹም የሆነ ሁለንተናዊ መረዳዳት ሲኖርና ከልብ መተሳሰብ ሲኖር ነው። ወንድ ልጅ ለሚስቱ ያለውን ፍቅር በሁለንተናዊ መልኩ ማሳየት ወይንም መግለጽ የማይችል አፋራም መሆን የለበትም። ሴት ልጅም ግልጽነት የጎደላት የውስጥ አጉረምራሚ መሆን የለባትም። በሁሉም፣ ስለሁሉም፣ የትም፣ መቸም፣ ግልጽና ግልጽ መሆን አለባቸው። ያ ከሆነ አንዱ ሌላውን የማወቅ፣ የመረዳት እድል ይኖራል። አንዱ የሌላውን አካሉን ስሜት ካወቀ ደግሞ ሁለንተናዊ የሆነ ተዋሕዶ ሊፈጠር ይችላል። ያም ትዳርን ያጸናዋል።

ሌላው ለጋብቻ ጽናት ወሳኙ ነገር ጸሎት ነው። ቤታችን የጸሎት ቤት ከሆነ ሕይወታችን ሁሉ ይባረካል። ቤታችንም የእግዚአብሔር ቤት ይሆናል። እግዚአብሔር እ

ራሱ የሆነለት ቤት ደግሞ መቸም ቢሆን ጽኑ ይሆናል። ስለዚህ በእውነተኛ የሕይወት አቅጣጫ በመጓዝ ራሳችን እንድንቀድስ የእግዚአብሔር ቃል ያስተምረናል።

**** በመምህር ልዑለ ቃል አካሉ***